# ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ፡ አጭር ዳሰሳ

**በኤደን ገረመው**

ሐበሻዊ ቃና መጽሄት ቅጽ 5

‹‹የአገር ውስጥ መጻሕፍት በማንበብ ቀበኛ ነበርኩ፡፡ የልቤን የሚያደርስልኝ ጽሑፍ ባጣ ጊዜ ልቤ ወደ ውጭዎቹ መጻሕፍት ሸፈተ፡፡ የኮበለለውን ቀልቤን ወደ አገር ቤት እንደገና የሰበሰበልኝ አንድ ጸሐፊ ነው፤ አዳም ረታ፡፡ ላለፉት አራት ዓመታት “ማኅሌት”፣ “ግራጫ ቃጭሎች”፣ “አለንጋ እና ምስር”፣ “እቴሜቴ የሎሚ ሽታ” እና “ከሰማይ የወረደ ፍርፍር” የተሰኙት መጻሕፍቱ እየተቀባበሉኝ ቆይቼያለሁ፡፡ አዳም በቅርብ ካሳተማቸው መካከል እንደ “እቴሜቴ ሎሚ ሽታ” እንቅልፍ ያስተወኝ መጽሐፍ የለም። ከልቤ ነበር የወደድኹት። “ከሰማይ የወረደ ፍርፍር” ግን እምብዛምም አልማረከኝ፡፡ የአዳም ስድስተኛ መጽሐፍ “ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ” በመጋቢት ወር ገበያ ላይ ሲውል ከማንም ሰው ስለመጽሐፉ እንዳልሰማ ተራውጬ አነበብሁት።

“ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ” እንደወትሮው ወደ አዳም የጽሑፍ ዓለም ከተተኝ። ጽሑፎች እንደተለመደው ስሜት ቀስቃሽ ናቸው። ለልቤ የቀረቡ ወዳጆቼ በሚመስሉኝ የአዳም ገጸ ባሕርያት ምክንያት አዳምን ራሱን የማውቀው ይመስለኛል፡፡ የማውቀውን እና የማስበውን ነገር ስለሚጽፍ የልብ አውቃ ይኾንብኛል፡፡ ነገሮችን የሚመለከትበት መንገድ ይመስጠኛል፡፡ ስለጋራ ሸንተረሩ ሳይኾን ዐይን የማይገቡ ስለሚመስሉቱ ሳር እና ጉንዳኑ ይመራመራል፡፡ ሽቶ ስለተርከፈከፈበት እና በፋሽን ስለተብለጨለጨው ሳይኾን በድስት ጥላሸት ስለጠቆረው ውበት ሲያወራ ይማርከኛል፡፡

በትክክልም ሐበሻዊ አስተሳሰብ፣ ሐበሻዊ ኑሮ የገባው፣ ከዛም አልፎ ሌሎች እንዲገባቸው ያደረገ ደራሲ ስለኾነ አዳም ለእኔ የተለየ ደራሲ ነው፡፡

ቀለል ያለ፣ የማይጎረብጥ እና ፍሰት ያለው አጻጻፉ ከመጻሕፍቱ እንዳልላቀቅ እና ደጋግሜ እንዳነባቸው ያደርገኛል፡፡ አዳም ለየት ያለ የአጻጻፍ ዘይቤ እንዳለው ሐያሲያን ሳይቀሩ የሚስማሙበት ነው፡፡ ስምንት አጫጭር ታሪኮችን የያዘው “ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ”ም በዚሁ የአጻጻፍ ስልት የታቃኘ ነው፡፡

**ባህር ማዶ**

የከዚህ ቀድሞቹን የአዳምን መጻሕፍት ያነበበ የደራሲው ብዕር እንደ ዋልያ በአገር ቤት ብቻ የተወሰነ እንደኾነ ይረዳል፡፡ አዳም በሚጽፋቸው ታሪኮች መዝጊያ ላይ መቼ እና የት እንደተጻፉ የማስፈር ልማድ አለው፡፡ አዲስ አበባም ተቀምጦም ኾነ ሆላንድ እና ካናዳ ከትሞ የጻፋቸው ሁሉም የሚያወሩት ስለ አገር ቤት ነው፡፡ ስለ ኢትዮጵያ፡፡ በአብዛኛው ደግሞ ስለ አዲስ አበባ፡፡ ከአዲስ አበባም ደግሞ የተወሰኑ አከባቢዎችን በመቼትነት በተደጋጋሚ ይጠቀማል፡፡ በ“ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ” ግን የአዳም ብዕር ባህር ማዶ ይሻገራል፡፡ ብዙዎቹ ታሪኮች ስደት ስደት የሚሸቱ እና በአገር ቤት ትዝታ የተሞሉ ናቸው፡፡

ከመጽሐፉ ውስጥ ረዥሙን የገጽ ብዛት የያዘው “ኩሳንኩስ” በተሰኘው ታሪክ በአዲስ አበባ፣ ናይሮቢ፣ ካናዳ እና እንግሊዝ ያሉ ስደተኛ ኢትዮጵያውያን ወጣቶችን ሕይወት ሰንቋል፡፡ አዳም ከሚደነቅባቸው ነገሮች አንዱ እጅግ በጣም የተራራቁና የማይገናኙ የሚመስሉ የተለያዩ ታሪኮችን በኾነች ስስ ግን ደግሞ ተዐማኒ በኾነች ነጥብ በማሠር የተያያዙ ታሪኮችን መፍጠር መቻሉ ነው፡፡ በዚህኛው ታሪክ ላይም ይህን የአጻጻፍ ዘይቤውን የበለጠ ተጠቅሞበታል፡፡ ስደት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ መጋረጃው ተገልጦለት ዐይኑን አፍጥጦ ወጥቷል፡፡

በወሬ ደረጃ የምንሰማው እና ሁላችንም የምናስበው የስደት ሕይወት ውስጥ የመሸጉ የሕይወት ኪሣራዎች በታሪኩ ውስጥ ቁልጭ ብለው ይታያሉ፡፡ አስመሳይነት፣ የሐበሻ ፖለቲካ እና ሐሜት ከስደት ፍቅር ጋራ ተሰናስለው ተቀምጠዋል፡፡ በዚህ ታሪኩ ላይ አዳም ከምላኅደል የራሱን የስደት ሕይወት በገጸ ባሕርያቶቹ ውስጥ እንደኮንትሮባንድ ሸሽጎ አስገብቷል ብዬ አምናለሁ፡፡ አዳም በ“ኩሳንኩስ” ውስጥ ሐበሻን “ከሌላው ዜጋ በበለጠ ታሪካዊ እንስሳ ነው” ሲል ይገልጸዋል፡፡ “ሐበሻ የሚያስበው ሲወለድ እናቱ ስላላሰችው ቅቤ ነው፡፡ እንደገናም ነገን ላግኝ ብሎ ዛሬን ሲጠላለፍባት፣ በፖለቲካ ሲናከስባት፣ ሲብጠለጠልባት፣ የሚመኛትን ነገን በዛሬ ሲያፈርስ ጊዜ ያልፍበታል” ይላል፡፡

የስደት ቡራቡሬ ቀለሞች ቀላል እና ማራኪ በኾኑ ኄራዎች ተነድፈው “ኩሳንኩስ” ውስጥ ተካትተዋል፡፡ እንደ “ኩሳንኩስ” ሁሉ “አሕዛብ ማድቤት በር ላይ” በተሰኘ ታሪኩ ላይም ስደትን አብጠልጥሎታል፡፡ ይህ ታሪክ ሙሉ ለሙሉ መቼቱ ለንደን ላይ ነው፡፡ ዋና ገጸ ባሕርይው ቆስጠንጢኖስ በድሮ ገርል ፍሬንዱ እና በአሁኗ ሚስቱ አማካኝነት ከአዲስ አበባ ጆሊባር ተነስቶ ለንደን ይገባል፡፡ በለንደን የሦስት ዓመታት ኑሮው ውስጥ እርሱንም ኾነ ባለቤቱን የማይመስል ልጅ መውለዱን እና የባለቤቱም ፀባይ እያደር መለወጡንም ያወጋናል፡፡ ቆስጠንጢኖስ ነገሮችን እየታዘበ ለራሱም ትንታኔ እየሰጠ በዝምታ ውስጥ ኾኖ ነገሮችን ያስቃኘናል፡፡

### የ “ያ ትውልድ” ፖለቲካ

የስደት ሕይወትን ማስቃኘት የጀመረው የአዳም ብዕር ዙሪያውን ይሸከርከርበት የነበረውን ፖለቲካንም ደፍሯል፡፡ አዳም ማኅበረሰባዊ እና ስነልቡናዊ ሐሳቦችን ውብ በኾነ ኹኔታ እያዋዛ ሲያሳየን የቆየ በመኾኑ እና እስከዛሬም እምብዛም ፖለቲካን ሳይነካ የቆየ በመኾኑ ስለ ፖለቲካ ሲጽፍ መገመቱ ሊከብድ ይችል ይኾናል፡፡ በስድስተኛው መጽሐፉ ግን ፖለቲካን ለየት ባለ ኹኔታ በመዳሰስ እና የተለየ ጭብጥ ይዞ በመነሳት አስደምሞናል፡፡ በስድሳዎቹ መጨረሻ እና በሰባዎቹ በነበሩ ወጣት ገጸ ባሕርያት ላይ ይበልጡኑ በመመርኮዝ የነበሩትን የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች እና በኅብረተሰቡ ላይ ያመጡትን ጫና እና የተውትን ዱካ ልቦለዳዊ በኾነ መንገድ ቀለል አድርጎ ሊያሳይ ሞክሯል፡፡

ለመጽሐፉ በርእስነት የተመረጠው “ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ”፣ “ኩሳንኩስ”፣ “ፍትፍትና ደጀሰላም”፣ “የመንግሥቱ ነዋይ ጊዜ” እና “ወላንሳ ወላንሳ መሃረቡሳ” በዚህ ጎራ የሚመደቡ ናቸው፡፡ “ይወስዳል መንገድ ያመጣል መንገድ” የሰባት መንገዶች ታሪክ ነው፡፡ በሳባቱም መንገዶች ላይ የሚያልፈው ዋናው ባለታሪክ ዓለሙ ከእናቱ ማሕጸን ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ ፖለቲካ ውስጥ ገብቶ ሕይወቱ እስከሚመሰቃቀልበት ጊዜ ድረስ ያለውን ህይወቱን በሰፊው ያትትልናል። እያንዳንዱ መንገድም በፎቶግራፍ ከመደገፉም በላይ በዓለሙ ሕይወት እና እድገት ላይ አንድ አንድ ደረጃን ይወክላል፡፡

የመጀመሪያው እና ከቤቱ እስከ ግቢው ያለው መንገድ የዓለሙን ልጅነት፣ የቤታቸው በአቧራ የተሞላ የእቃ አቀማመጥ የእናቱ ደማቅና ዝነኛ የቡና ሥነ ሥርዐት፤ እንደዚሁም የጎረቤቶቹን ሕይወት ይወክላል፡፡ ሁለተኛው መንገድ ከግቢው በር ጀምሮ ወደ ሰፈሩ ኮረኮንች ድረስ የሚዘልቅ ነው፡፡ አብሮ አደግ እህትማማች ጎረቤቶቹን፣ ሽማኔ አባቱን እና ሕይወታቸውን እንደዚሁም የታላቅ እህቱን ድንገተኛ ሞት የሚተረክበት ክፍል ነው፡፡

ሦስተኛው መንገድ የጉርምስና መጀመርን አብሣሪ ነው፡፡ ከብይና ከአቧራማ ሜዳ ኳስ ጨዋታ በተረፈው የጥናት ሰዓት ላይ ሰርጎ በገቡ ጽሑፎች አማካይነት ስለገበየው የፖለቲካዊ እውቀት ያወጋናል፡፡ ይህንም እውቀት ተጠቅሞ ለሙብት ለመቆም ይሞክራል፡፡ የእርሱ ጩኸት የላብ አደሩ ብቸኛ ድምፅ፣ ያለ እርሱም ምን ለውጥ የማይመጣ፣ እርሱም ብቸኛው የላብ አደሩ ሙብት አስከባሪ የኾነ ሲመስለው እናያለን፡፡ “አምባገነናዊውን ፋሽስታዊ የምርጥ መኮንኖች መንግሥት” ለመጣል ቃል የገባበትን እና በሌሊት የኤሌክትሪክ ምስሶዎች ላይ ተቃውሞውን ያሰፈረበትን ጊዜ ይዳስሳል፡፡ ከፖለቲካ ጎን በእንስት ፍቅር የተነደፈበትን ጊዜ ይወክላል፡፡

በአራተኛው፣ በአምስተኛውና በስድስተኛው መንገዶች ላይም ገጸ ባሕርይው በኖረበት በሰባዎቹ ውስጥ የነበረውን ወጣትነት፣ ጓደኝነት እና ፖለቲካዊ ሕይወት ያስቃኛል፡፡ በፖለቲካ የመቆራቆሱ ዳፋ ለፍቅረኛም እንደሚተርፍ መራሩን እውነት ይግተናል፡፡ የፍቅረኛውን ሴትነት አውቆ የፈነጠዘ ወጣት መልሶ ደግሞ በፖለቲካዊ አቋም ልዩነት ምክንያት እርሷን አሳልፎ ለሞት ሲሰጥ ያሳየናል፡፡ ከጓደኞቹ ጋር ኢንተርናሲዮናል የዘመረበትን ወቅት፣ ድንጋይ የወረወረበትን፣ ጥይት የተኮሰበትን በመልሱም በወፌላላ የተገረፈበትን ሂደት በዝርዝር ይተርካል፡፡ በፖለቲካዊ ጦስ ምክንያት በሱዳን አድርጎ እንግሊዝ አገር የገባበትን መንገድ ያስጎበኘናል፡፡

በሰባተኛው እና በመጨረሻው መንገድ የታሪኩ ምጸት የሚታይበት ነው፡፡ ዋና ገጸ ባሕርይ የተዋጋበት ዓላማ እና ሐሳብ ውጤት እና ትርጉም ሲያጣበት ያሳያል፡፡ ደም ባፈሰሰበበት እና ደሙ በፈሰሰበት ያለፈው ሕይወቱ ይቆጫል፡፡ የወጣትነት ጓደኛው በስደት ፖለቲካ ተተብትቦ እርሱን በታቃራኒ ጎራ ይፈርጀዋል፡፡ አዳም የያን ትውልድ ፖለቲከኞች እና በፖለቲካ ምክንያት ተሰድደናል የሚሉ ወጣቶችን በሰላ ብዕሩ ይወርፋቸዋል፡፡ አነሳሳቸው እና አጨራረሳቸው ለየቅል የመኾኑ እውነታ በሕይወታቸው ውስጥ ያመለክታል፡፡ ፖለቲካዊ ምልከታው ከሰባዎቹ ተሻግሮ 2075 ድረስ ይስፈነጠራል፡፡

**ምናባዊው አዳም**

አዳም በ2075 ዓ.ም ኢትዮጵያ ምን እንደምትመስል በምናቡ የሳለውን በ"ወላንሳ ወላንሳ/ መሐረቡሳ" አቅርቦልናል፡፡ ይህ ታሪክ የመጽሐፉ መደምደሚያ ሲኾን ከሁሉም ታሪኮቹ በበለጠ በብዙ የሕዳግ መረጃዎች የተደገፈ ነው፡፡ በዚህ ታሪክ ኢትዮጵያ ሰውነታቸው ልክ እንደ ወንድ ሙሉ ለሙሉ በጸጉር የተሸፈኑ ሴቶች እና ከእነሱ በሚወለዱ ልጆች እንዲሁም የእነርሱ ተቀናቃኞች በኾኑትና ሰውነታቸው መላጣ በኾኑት ፓርቲ ተከፋፍላ የምትገዛ አድርጎ ያሳየናል፡፡ ባለጸጉራሞቹ "ጠጋዎች/ጸጋዎች" ሲላቸው መላጣዎቹን ደግሞ "መነኖች" ሲል ሰይሚቸዋል፡፡ አገሪቷን ባለሙሉ ሥልጣን በመኾን የሚገዙት ጠጋዎች በሚያወጧቸው አወዛጋቢ ሕጎች እና በሚከተሉት የርዕዮተ ዓለም አቋም ምክንያት የሚፈጠረውን ኹኔታ ታሪኩ በምናብ ያስቃኛል፡፡

ታሪኩ የሚጀምረው የ2075 ዓ.ም የኢትዮጵያውያን የዘመን መለወጫ ዋዜማ በዓል ላይ ነው፡፡ አዲስ አበባ ከሚያረሰርሳት ዝናም ጀምሮ ሁሉ ነገሯ የተበከለ ኾና ተስላለች፡፡ መንገዶቿ በላስቲክ ብጥስጣሾች እና በእንስሳት እና የሰው ዐይነ ምድር የተሞላ፣ በፋብሪካዎች ጭስ ዓየሯ የተበከለ እንደሚኾን አዳም ይተነብያል፡፡ የውኃ ቧንቧ ካየች ብዙ ጊዜዋ በመኾኑ ሰዎች ገላቸውን የሚታጠቡትም ኾነ ምግባቸውን የሚያበስሉት በሦስት ደረጃዎች በተከፈለ ሀሁእ /H2O ወይም አንድ ሃይድሮጅን አንድ ኦክስጂን/ የተሰኘ ውሃ ከፋብሪካዎች በመግዛት ነው፡፡ ለውሃ እጥረት በምክንያትነት ከተጠቀሰው አንዱ ደግሞ ሙሉ አዲስ አበባን ያጠጣል የተባለውም የደዴሳ ግድብ በተጠናቀቀ በሳምንቱ በሱዳንና በግብጽ አየር ኀይል መመታቱ ነው፡፡

በሁለት ሺሕ ሰባ አምስት ዓ.ም በሚፈጠረው የዓየር ብክለት 'የውኃ ችግርና የከተማ ንጽሕና ጉድለት ምክንያት ከሰባ በመቶው በላይ ሕዝብ በሳይነስ እና በተለያዩ የመተንፈሻ አካላት በሽታዎች በመጠቃቱ ወላንሳ የተባለው የመሐረብ ዐይነት ከፍተኛ የኾነ ተፈላጊነት እንዳለው ደራሲው ይነግረናል፡፡ በዚህም ምክንያት ኢትዮጵያንም የዓለም ኅብረተሰብ "The land of thirteen handkerchiefs" ወይም "የዐሥራ ሦስት መሐረቦች አገር" በማለት እንደሚጠሯት ይገልጻል፡፡ ታዋቂ ሚድያዎችም "A land where nothing is harvested by the people, except their nasal fluids" ወይም "እዚያ አገር ያሉ ሰዎች ካፍንጫቸው ፈሳሽ ውጪ ምንም ምርት የማያመርቱ ናቸው!" ሲሉ እንደሚሳለቁ ያስነብባል፡፡ በሽታው ፍጹም የለም ሲል የሚያስተባብለው የጸጋዎች መንግሥት ግን ነገሩን እንደስድብ ከመቁጠር ይልቅ እንዲያውም የአገሪቱ ሰዎች "ልዩ" በመኾናቸው የመጣ እንደኾነ ይገልጻል፡፡

የጸጋ መደብ አባል የኾነችው የዚህ ታሪክ ዋና ገጸ ባሕርይ ከአንድ መነን ጋራ ባሳለፈችው የፍቅር ሕይወት ምክንያት እና ባላት አፈንጋጭ ፖለቲካዊ አመለካከት ከመደቧ አባላት የሚደርስባትን የማግለልና የጸጥታ ሰዎች ክትትል በተከታይነት ይተርካል፡፡ ይህ የጸጥታ ሰዎች /ሴኩዎች/ ክትትል ካፌ ውስጥ እና የሕዝብ ትራንስፖርት ሰልፍ ላይ ጭምር የማይቀር ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ኅብረተሰቡ የሚናገረው ተራ ነገር ሁሉ ወደ ሌላ እንዳይተረጎምበት በጸጥታ የሚታሠር ዐይነት ይኾናል፡፡

አዳም በዚህ ታሪኩ የምንኖርበትን እና የአሁኑን ዘመን የአገራችንን ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ኹኔታዎች እንደዚሁም የማኅበረሰብ እና ሥነ ምግባራዊ ግድፈቶችን የተቸተበት ነው ባይ ነኝ፡፡ አሁን ያለው ጉራማይሌ ቋንቋ አጠቃቀማችን እንዲሁም የዓየር ብክለት በዚሁ ከቀጠሉ ወዴት እንደሚያመሩ ያመላከተበት ነው፡፡ በታሪክ ውስጥ የተጠቀሱት አብዛኞቹ ነገሮችም እስከ 2075 ዓ.ም ድረስ መቆየት ሳይጠበቅብን ዛሬውኑ ምልክቶቻቸውን እያየን ነው።

**የምልኪ ቅጽበት**

አዳም ይህን ጽሑፍ ጨምሮ በስምንቱም አጫጭር ታሪኮቹ ውስጥ የሚታይ ተመሳሳይ እና ታሪክ ቀያሪ ቅጽበት ተጠቅሟል፡፡ ቅጽበቱም በእያንዳንዱ ታሪክ ውስጥ ከሦስት እና ከአራት መሥመር በማይበልጥ ኹኔታ ተቀምጧል። ይህ ቅጽበት በእንግሊዘኛው "Omen" ወይም ደግሞ በአማርኛ/ኦሮምኛ/ "ምልኪ" የሚባለው ነው፡፡

ድሮ ድሮ እናቶቻችን ወደገበያ ሲሄዱ ከሚያጋጥማቸው ወፍ በመነሳት "ዛሬ ገዴ ነው" ወይም ደግሞ "ወፍ ነገረችኝ፣ መልካም ቀን አይደለም" ብለው ለመሄድ ወይም ላለመሄድ ይወስኑ ነበር፡፡ አሁንም ድረስ በገጠር አከባቢዎች ይህ አመለካከት አለ፡፡ አዳም ይህን የምልኪ አስተሳሰብ በሌላ መልኩ በየታሪኮቹ ለማሳየት ሞክሯል፡፡ አዳም በስምንቱም ታሪኮቹ ይህን ምልኪ የገለጸው በአሞራ መልኩ ነው፡፡ ነገርየው አሞራ ይባል እንጂ ከተለመደው አሞራ በብዙ እጅ የሚገዝፍና እንደሰው አተኩሮ የሚያይ እና የሚያነጋግር የሚመስል፣ የኩንቢው ግማሹ ደም የመሰለ፣ ላባውም የሚያብለጨለጭ ነው፡፡ ይህ አሞራ በሕይወታቸው ከተከሰተ በኋላ የታሪኮቹ ዋና ገጸ ባሕርያት ሕይወታቸው ይቀየራል፡፡

በ "የመንግሥቱ ነዋይ ጊዜ" በሚለው ታሪክ ውስጥ አሞራው ሁለት ጊዜ ይከሰታል። አንደኛው ዋና ገጸ ባሕርይው ሰፈር ውስጥ የኡኡታ እና የብጥብጥ ድምፅ ሰምቶ በወጣ ጊዜ የሚያጋጥመው ነው። ሁለተኛው ደግሞ የዋናው ገጸ ባሕርይ አባት በጥይት ተመትቶ ወድቆ ባለበት አሞራውን መመልከቱ ነው። "ፍትፍት እና ደጃ ሰላም" ላይም አሞራው እንዲህ ተጠቅሷል። "በሁለቱ ቤቶች መሀል ቀድሞ ልብ ያላልኹት ትልቅ ዛፍ አለ። የዚህ ዛፍ ጫፍ ተለምጧል። እዚያም ላይ ምናልባት አምስት ሜትር ስፋት ያላቸው ክንፎች ያሉት አሞራ ሚዛኑን ለመጠበቅ ይጣጣራል። ክንፎቹ የቆምኩበት ድረስ የሚሰማ ነፋስ ያነሳሉ . . . .ፍም የመሰሉ ዐይኖቹ ይታዩኛል። እንደ መጀመርያው ከመደንገጥ ይልቅ ባልገባኝ ምክንያት ሁለመናዬ ተረጋጋ። ላፍታ ይጠዘጥዘኝ የነበረው የግንባሬ ቁስል ተረሳኝ።"

"ኩሳንኩስ/ እንደገና ሊጥ" በሚለው ታሪክ ውስጥ ደግሞ አሞራው የሚናገር መስሎ ተስሏል። "{አሞራ} ዐይኖቹ የሰው ይመስላሉ። ሽፋሽፍት ያለው አሞራ ዐይታ አታውቅም። በድንጋጤ አፏን ስትይዝ ከውስጧ ይኹን ከውጭ (ምናልባት አሞራው) "አይዞሽ!" የሚል ቃል የሰማች መሰላት። ቃሉ ላይ አተኮረች። የቃሉ መነሻ ከየት እንደኾነ ለመረዳት ዐይኖቿን ጨፍና ስትፈልግ ቀዝቃዛ ዐየር በላይዋ ላይ አለፈ። "አሕዛብ ማድቤት በር ላይ"ም የዚሁ የአሞራ እንደ ሰው ተናጋሪነት ዳግም ይመጣል። "አሞራው ከጉልላቱ ላይ በሚያስገርም ግርማ ተነሳ። ባለኹበት ሕንፃ ላይ በቀስታ ሲያልፍ ልክ እንደ ሰው በዐይኖቹ እየተከተለኝ ነበር። ወደ ጀርባ ከመሰወሩ በፊት ኩንቢው በትንሹ በትንሹ ተነቃነቀ። ድምፅ የሰማሁ መሰለኝ። ከአሞራው ኩምቢ ሲወጣ የተሰማኝ የወፍ ዜማ ወይም የተለየ የአራዊት ድምፅ ሳይኾን ከባድ የሰው ትንፋሽ የመሰለ ነገር ነው። እዚህም ትንፋሽ ውስጥ የኾነ ቃል ነበር። ቃሉ ዙርያውን በትንፋሽ ስለተጠቀለለ በግልጽ ምን እንደተናገረ ባይሰማኝም ብቻ 'ግባ' የሚል መሰለኝ።" በዚህ ታሪክ ላይ ያለው ገጸ ዋና ገጸ ባሕርይ የአሞራውን ምክር ሰምቶ ወደ ቤት ሲገባ ሕይወቱን ጨርሶ ሊለውጥ የሚችል ድርጊት ይመለከታል።

እንዲህ አሞራ ያንዣበበባቸው የአዳም ስምንቱም ታሪኮች በቀላል ቃላት እና ሂደት ሐሳብን፣ ሕልምን፣ ትካዜን እና ምኞትን የከተበበባቸው ናቸው። ሰው ሰው የሚሸቱ እና ውስጣችንንም የሚኮረኩሩ ናቸው። ለዚያም ይመስላል በሐሳብ ፣ በሕልም፣ በምኞት እና በትካዜ ባህር ውስጥ እያሰጠመ፣ ወደ ኋላ እና ወደ ፊትም እያስጓዘ ቅኔ በሚመስል አኳኋን ሐሳቡን ያስቀመጠው።